# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

# 29 ኛ ሳምንት

# ቅዱስ ጊዮርጊስ

**ዓላማ**

- ጽናትና እምነትን ከቅዱስ ጊዮርጊስ ታሪክ መማር።

**ምንባብ**

- ገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ዕብ. 11÷1- ፍ/ም

**መግቢያ**

- ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስለተባለ ቅዱስ እንማራለን።
- ቅዱስ(ቅድስ) ሕይወታቸውን በቅድስና ሕይወት የመሩ፣ ዓላማዊ ምኞትን ክደው (ትተው) ራሳቸውን በጸሎት፣ ሌሎችን በመርዳት እና በሌሎችም መንፈሳዊ ሥራዎች የተሠማሩ ናቸው።

**ትምህርቱ**

- ቅዱስ ጊዮርጊስ ልዳ በተባለ ቦታ ተወልደ።ሃያ(20) ዓመት ሲሆነው ቤሩት ወደምትባል ከተማ ሄደ።በዚያም የቤሩት ሕዝቦች የሚያመልኩት ዘንዶ ነበር።
- ወደ ከተማው ከመግባቱ በፊትም በዛፍ ላይ የታሰረች ሴት ልጅ አየ።
- ምን እንደሆነች ሲጠይቃትም ለሚያመልኩት ዘንዶ በመሥዋዕትነት መቅረብዋንና እርሱም ፈጥኖ ካልሄደ ዘንዶው ከመጣ እርሱንም እንደሚበላው ነገረችው። ቅዱስ ጊዮርጊስም ይሄን ክፉ ነገር እንደማይፈራ ነገራት።
- ዘንዶው ቅዱስ ጊዮርጊስን ሲያየው ሊገድለው አንገቱን ቀና አደረገ።ቅዱሱ ግን ***"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሃዱ አምላክ"*** ብሎ በመስቀል ምልክት አማተበበት።
- ዘንዶውም ደካማ ሆኖ መሬት ላይ ወደቀ።ከዚያም ቅዱስ ጊዮርጊስ ፈረሱን አምጥቶ፣ የታሰረችውን የገዢውን ልጅ ጫናት፣ዘንዶውንም በገመድ አሥረው እየጎተቱ ወደ ከተማ አስገቡት።
- የቤሩት ሰዎች ይሄንን ሲያዩ፣ደንግጠው ቅዱስ ጊዮርጊስን ለምን ወደ ከተማው አመጣህብን አሉት። ቅዱስ ጊዮርጊስም ዘንዶው አምላክ እንዳልሆነና ምንም ኃይል እንደሌለው ነገራቸው በክርስቶስ እንዲያምኑም አስተማራቸው። ሲያመልኩት የኖሩትን ዘንዶም ገደለው።
- ስለ ክርስቶስ የሰበከላቸውን ከሠሙ በኋላም÷ክርስትናን አምነው ተቀበሉ። የመጀመሪያው ትዕዛዝ እግዚአብሔር በፍጹም ልብ መውደድና ከርሱ ሌላ አለማምለክ ነው።የቤሩት ሰዎች ዘንዶውን ያመልኩ ነበር። ሰማዕቱ ግን ዘንዶውን ገድሎ ክርስቶስን እንዲያመልኩ አደረገ።
- የሰማዕቱ ጸሎት ከክፉ ይጠብቀን ይርዳንም አሜን!!

**መዝሙር**

ጊዮርጊስ ኃያል መስተጋድል (2)

ገባሬ ተዓምር (2) ኮከበ ክብር(2)

# St George kills the drgaon by the power of the Cross



ይቆየን።